# የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት አሠራርን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 855/2014

A Directive Issued to Determine the Operation of the Tax Appeals Office (Directive No. 855/2014)

የገቢዎች ሚኒስቴር
Ministry of Revenues

ታኅሣሥ 17፥ 2015

## መግቢያ

ታክስ ከፋዮች በያሉበት ቅ/ጽ/ቤት በታክስ ውሳኔ ላይ ያላቸውን ቅሬታ ማቅረብ የሚችሉበት ተደራሽነት ያለው፣ በአግባቡ የተደራጀ፣ የተቀላጠፈና ፍትሐዊ የሆነ የውሳኔ ሐሳብ የሚያቅርብ የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት በማደራጀት የታክስ ከፋዮችን ቅሬታ ለመፍታት የሚያስችል ወጥነት ያለው የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ታክስ ከፋዮች የሚያቀርቡትን የግብር ውሳኔ ቅሬታ በወቅቱና በቅርበት ባለ መረጃና ማስረጃ ለመወሰን፤ ተገቢው ውሳኔ ተወስኖ መከፈል ያለበት ታክስ ቶሎ ወደ ገቢ እንዲቀየር ለማስቻል፤ ታክስ ከፋዩ የታክስ ውሳኔ ቅሬታውን የሚያቀርበው በሚኒስቴሩ በሚወሰንበት የታክስ መጠን በተዋረድ ተከፍሎ በተለየ ሁኔታ ሳይሆን የሚያቀርበውን ቅሬታ መሰረት በማድረግ ታክስ ከፋዩ ባለበት ቅ/ጽ/ቤት ቅሬታውን በማስተናገድ ፍትሐዊነትን ለማስፈንና በታክስ መጠን ያልተገደበ እኩል ተገልጋይነትን ለማረጋገጥ ተገቢ በመሆኑ፤

በታክስ ውሳኔ ላይ ቅሬታዎች የሚታዩበትን የቅሬታ አቀራረብና ምርመራ እንዲሁም የውሳኔ ሐሳብ አቀራረብና የውሳኔ አሰጣጥ ሥርዓት እና የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት ሥልጣንና ተግባርን ለመወሰን የወጣውን መመሪያ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ሚኒስቴሩ በፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ "**የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት አሠራርን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 855/2014**" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም፦

1/ **"ሚኒስቴር"** ወይም **"ሚኒስትር"** ማለት የገቢዎች ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፡፡

2/ **"ጽ/ቤት"** ማለት በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በአዋጁ አንቀጽ 55 (1) መሠረት የሚደራጅ የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት ነው፡፡

3/ **"አዋጅ"** ማለት የፌደራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ሲሆን አዋጁን ለማስፈፀም የወጣውን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 407/2009 ይጨምራል፡፡

4/ **"የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት"** ማለት በሥሩ ባለሙያዎችን፣ የጽ/ቤቱን ኃላፊና ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞችን የያዘ የሥራ ክፍል ነው፡፡

5/ **"የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት ኃላፊ"** ማለት የጽ/ቤቱ አስተባባሪ ወይም የጽ/ቤቱ ምክትል ሥራ አስኪያጅ ማለት ነው፡፡

6/ **"ቡድን"** ማለት ባለሙያዎችን፣ የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት ኃላፊን ወይም ሰብሳቢውን እንደሁኔታው የጽ/ቤቱን ምክትል ሥራ አስኪያጅ እና የጽ/ቤቱን ፀሀፊ የያዘ ስብስብ ነው፡፡

7/ በዚህ መመሪያ ውስጥ ያሉ ሌሎች ቃላትና ሐረጎች በታክስ ሕግ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

8/ በዚህ መመሪያ ውስጥ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀ የሴት ፆታንም ያካትታል፡፡

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በፌደራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 መሠረት የታክስ ውሳኔን በመቃወም በሚቀርብ ቅሬታ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

## የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤትን ስለማደራጀት

## 4. የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት አደረጃጀት

1/ በታክስ ውሳኔ ላይ የሚቀርብ ቅሬታን አጣርቶ የውሳኔ ሐሳብ ለሥራ አስኪያጅ ወይም እሱ ለወከለው የሥራ ኃላፊ የሚያቀርብ የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት በሁሉም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እንደሚከተለው ይደራጃል፤

ሀ/ የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት ኃላፊ፣

ለ/ የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት ባለሙያዎች፣

ሐ/ የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት ፀሀፊ፣

መ/ የጽ/ቤቱ ሪከርድ ሥራ አመራር ሁለገብ ባለሙያ እና

ሠ/ የጽ/ቤቱ ረዳት እና እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ሁለት የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት አስተባባሪዎች እና የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት ምክትል ሥራ አስኪያጅ ይኖሩታል፡፡

3/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በቅ/ጽ/ቤቶች ሥር የሚደራጀው የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት ያለበት የሥራ ጫና እና ሌሎች ጉዳዮች ታይተው እንደ አስፈላጊነቱ ሚኒስትሩ ሲፈቅድ ከአንድ በላይ ቡድን ሆኖ ሊደራጅ ይችላል፡፡

## 5. <u>የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ቡድን ሰብሳቢዎች አሰያየም</u>

1/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4(3) መሠረት ከሁለት በላይ የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ቡድን የሚደራጅ ከሆነ የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት አስተባባሪ ለቡድኖች ሰብሳቢ ይሆናል፡፡

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ለሚገኘው የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት የጽ/ቤቱ ምክትል ሥራ አስኪያጁ ለቡድኖች ሰብሳቢ ይሆናል፡፡

## 6. <u>የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት ተጠሪነት</u>

1/ የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት ተጠሪነቱ ለቅ/ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጅ ነው፡፡

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እንደተጠበቀ ሆኖ እያንዳንዱ የቅ/ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጅ ከታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት የሚቀርብለትን የውሳኔ ሐሳብ መርምሮ ማፅናት፣ መለወጥ፣ ማሻሻል እንዲችል በዚህ መመሪያ ውክልና ተሰጥቷል፡፡

## 7. <u>የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት ሠራተኞች አመዳደብ</u>

1/ በታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት የሚሰራ ባለሙያ ተፈላጊው የትምህርት ዝግጅት፣ ተፈላጊው ችሎታና የሥራ ልምድ ማሟላቱ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ በኩል ተረጋግጦ ሲቀርብ በተቋማዊ አቅምና ድጋፍ ዘርፍ አማካኝነት እንዲመደብ ይደረጋል፡፡

2/ ተፈላጊውን መስፈርት የሚያሟላ ባለሙያ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ካልተገኘ፣ ተፈላጊውን መስፈርት የሚያሟላ ባለሙያ በተቋማዊ አቅምና ድጋፍ ዘርፍ አማካኝነት ከዋናው መስሪያ ቤት ወይም ከሌላ ቅ/ጽ/ቤት ተውስዶ ይመደባል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተደነገገው ቢኖርም ተፈላጊውን የትምህርት ዝግጅት፣ ተፈላጊውን ችሎታና የሥራ ልምድ የሚያሟላውን ባለሙያ ሚኒስትሩ ከየትኛውም ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አወዳድሮ ሊመድብ ይችላል፡፡

4/ በሥራ ክፍሉ የሚመደቡ ባለሙያዎች በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኦዲት፣ በታክስ አወሳሰን እና በሕግ ሙያ ያገለገሉ መሆን ያለባቸው ሲሆን በቡድኑ ውስጥ ካሉ ባለሙያዎች፣ አንድ የሕግ ባለሙያ እና ቢያንስ አንድ የሂሳብ አያያዝ ባለሙያ መኖር አለበት፡፡

5/ በታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት የተመደበ ባለሙያ ወይም ሠራተኛ ወይም የጽ/ቤቱ ኃላፊ ከአቅም በላይ በሆነ አስገዳጅ ምክንያት በሥራ ቦታ በማይገኝበት ጊዜ የቅ/ጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ በጊዜያዊነት ለጽ/ቤቱ ኃላፊ ወይም ባለሙያ ወይም ሠራተኛ ሊመድብ ይችላል፡፡

6/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት በጊዜያዊነት የተመደበ ኃላፊ ወይም ባለሙያ ወይም ሠራተኛ ከስድስት ወር በላይ በጊዜያዊነት ሊሰራ አይገባም፡፡

7/ የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት ሠራተኞችንና ባለሙያዎችን እንዲሁም የጽ/ቤት ኃላፊውን ዝውውር፣ ምደባ እና የደረጃ ዕድገት በሚመለከት የሚኒስቴር መ/ቤቱ አግባብነት ያላቸው መመሪያዎች እና የአደረጃጀት ጥናቶች ተፈጻሚ ይደረጋሉ፡፡

## ክፍል ሦስት

### የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት

8. <u>የጽ/ቤቱ ሥልጣን</u>

1/ በታክስ ከፋዩ የቀረበ ቅሬታን በነፃነት እና በሕግ መሰረት በመመርመር በቅሬታ ላይ የውሳኔ ሐሳብ ለቅ/ጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ ወይም እሱ ለወከለው የሥራ ኃላፊ ያቀርባል፡፡

2/ በታክስ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ታክስ ከፋይ የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ እንዲደርሰው ከተደረገበት ቀን ቀጥሎ ካለው የሥራ ቀን ጀምሮ በሚቆጠር በሃያ አንድ ቀናት ውስጥ በውሳኔው ላይ የቅሬታ አቤቱታ ያቀረበ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

3/ ጽ/ቤቱ ታክስ ከፋዩ ያቀረበው ቅሬታ የታክስ ውሳኔውን የሚቃወምበትን ምክንያትና የሚጠይቀውን ዳኝነት የሚገልጽ መሆኑን እንዲሁም ተገቢነት ያላቸው ሰነዶችን አያይዞ ያቀረበ መሆኑን በማረጋገጥ ቅሬታውን ይቀበላል፡፡

4/ ታክስ ከፋዩ ቅሬታ ባቀረበበት የታክስ ውሳኔ ላይ ያመነው ካለ በቅድሚያ ያመነበትን ታክስ ስለመክፈሉ ወይም የክፍያ ስምምነት ስለማድረጉ ማስረጃ መቅረቡን ያረጋግጣል፡፡

5/ የቀረበው የታክስ ውሳኔ ቅሬታ ሲመረመር በታክስ ስሌት የተመለከተው የታክስ መጠን ሊጨምር ይገባዋል የሚል እምነት የሥራ ክፍሉ ሲኖረው፣ የታክስ ስሌቱ በሚመለከተው አካል እንደገና እንዲታይ ለሥራ አስኪያጁ ወይም እሱ ለወከለው የሥራ ኃላፊ የውሳኔ ሐሳብ ያቀርባል፡፡

6/ የሥራ ክፍሉ የተጣለበትን ኃላፊነት ባለመወጣት ጥፋት ሰርቶ ቢገኝ አግባብ ባለው ሕግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## 9. የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት ኃላፊ ተግባርና ኃላፊነት

1/ የጽ/ቤቱ ኃላፊ የጽ/ቤቱን ዕቅድ ያዘጋጃል፤ ባለሙያዎችን ይመራል፣ያስተባብራል፤ ጽ/ቤቱ በሰው ኃይል እና በቁሳቁስ እንዲሟላ ያደርጋል፡፡

2/ ጽ/ቤቱ በሚያደርገው የቅሬታ ማጣራት ሂደት ከቅሬታው ጋር ተያያዥነት ያላቸው መረጃዎችና ማስረጃዎች ከሚመለከተው የሥራ ክፍል እንዲቀርብለት ሊጠይቅ ይችላል፡፡ የተያዘው ጉዳይ የሕግ ወይም የሙያ ማብራሪያ የሚያስፈልገው ከሆነ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ከሕግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ወይም ከሚመለከተው የሥራ ክፍል ማብራሪያ እንዲሰጥበት ያደርጋል፡፡

3/ በታክስ ውሳኔ ቅሬታ ማጣራት ሂደት ላይ የሚገኙ ጉዳዮችን በሚመለከት ወይም ከታክስ አወሳሰን ጋር በቀጥታ ወይም ቀጥታ ባልሆነ መንገድ ግንኙነት ያለውን ማንኛውንም ሰው ወይም አካል በመጥራት መረጃ ይቀበላል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሙያዊ ምክር ይጠይቃል፡፡

4/ በጽ/ቤቱ ተጣርቶ የቀረበ የውሳኔ ሐሳብ በቃለ-ጉባዔ በማስደገፍ ለቅ/ጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ ወይንም እሱ ለወከለው የሥራ ኃላፊ ያቀርባል፡፡

5/ የጽ/ቤቱን ባለሙያዎችና ሠራተኞች የሥራ አፈፃፀም ይመዝናል፤ የክፍሉን የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት ለቅ/ጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ እና ሪፖርቱ ሊደርሳቸው ለሚገቡ ሌሎች አካላት በወቅቱ እንዲላክ ያደርጋል፡፡

6/ በጽ/ቤቱ የተሰጠው የቅሬታ ላይ ውሳኔ ለቅሬታ አቅራቢውና ቅሬታው ለሚመለከተው የሥራ ሂደት ወይም ቡድን እንዲሁም ለሚመለከታቸው አካላት በሙሉ እንዲደርሳቸው ያደርጋል፤ ውሳኔው በአግባቡ ተፈፃሚ መሆኑን ይከታተላል፡፡ በውሳኔው መሰረት ካልተፈፀመ ለሥራ አስኪያጁ እና ለቅ/ጽ/ቤቱ ተቋማዊ ስጋት ሥራ አመራርና ሥነ-ምግባር በማሳወቅ ተገቢውን እርምጃ ያስወስዳል፡፡

7/ የጽ/ቤቱ ሠራተኛ ወይም ባለሙያ በማናቸውም ምክንያት በዘላቂነት በተመደበበት የማይኖር ከሆነ ሌላ ሠራተኛ ወይም ባለሙያ እንዲመደብ ለቅ/ጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ ያሳውቃል፡፡

8/ ለጽ/ቤቱ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን በማደራጀት፣ ጥናትና ትንተና በማድረግ የችግሩን መነሻና የመፍትሄ ሐሳብ ያካተተ ሪፖርት ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ እና ሪፖርቱ ለሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች ያቀርባል፡፡

9/ የቅሬታ አቀባበልና አፈታትን ለማፋጠን የሚያስችሉ አሠራሮችንና የሥራ ማንዋሎችን በዋናው መስሪያ ቤት ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

10/ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ አደራጃጀት የተቀመጡትን የወል የሥራ ኃላፊነቶችን ይወጣል፡፡

11/ በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሥር ለሚገኘው የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት ምክትል ሥራ አስኪያጅ የሆነ ሰው በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 10 የተዘረዘሩትን ተግባርና ኃላፊነቶች ያከናውናል፤ይወጣል፡፡

10. <u>የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት ፀሀፊ ተግባርና ኃላፊነት</u>

1/ በታክስ ውሳኔ ላይ ለጽ/ቤቱ የሚቀርብ ቅሬታን በቅሬታ የማቅረቢያ ጊዜ ገደብ እና በታክስ አስተዳደር ሕጉ መሰረት መቅረቡን በማረጋገጥ ይቀበላል፤

2/ ከጽ/ቤቱ ኃላፊ ጋር በመመካከር የስበሰባ አጀንዳ ያዘጋጃል፣ የስበሰባ ቃለ-ጉባዔ ይይዛል፤

3/ በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት በቀጥታ ያለ ድምፅ ይሳተፋል፤

4/ የቀረቡ ቅሬታዎችን በቅሬታ አቅራቢው ሥም በተከፈቱ ማህደሮች መዝግቦ ይይዛል፤

5/ የጽ/ቤት ኃላፊው የሰጠውን አመራር በመፈጸምና የተዘጋጁ ሪፖርቶችን ወጪ በማድረግ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፤

6/ ቅሬታ የቀረበበት ጉዳይ ተጨማሪ ማስረጃ መሰባሰቡን ይከታተላል፣ ደብዳቤዎች በወቅቱ እንዲደርሱ ያደርጋል፣ ቅሬታ አቅራቢና ቅሬታ የቀረበበት አካል በቀረበው ጉዳይ እንዲያስረዳ ቀጠሮ ይሰጣል፣ ይከታተላል፤

7/ የውሳኔ ሐሳብ ረቂቅ በማዘጋጀት ተፈርሞ በዕለቱ ለኃላፊ እንዲደርስ ያደርጋል፣ ከኃላፊው ጋር በመመካከር የቅሬታ ላይ ውሳኔው ለቅሬታ አቅራቢው እና ቅሬታ ለቀረበበት አካል እንዲደርስ ያደርጋል፣አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

8/ በቀረበ የታክስ ውሳኔ ቅሬታ ላይ የተሰጠውን የቅሬታ ላይ ውሳኔ እና የውሳኔው ግልባጭ ለሚመለከታቸው አካላት በአስቸኳይ እንዲደርስ ያደርጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

9/ የአፈፃፀሙ ሪፖርት በወቅቱ ተዘጋጅቶ በጽ/ቤት ኃላፊው ተፈርሞ ለሚመለከታቸው አካላት በሪፖርት ማቅረቢያ ጊዜ ገደብ እንዲደርስ ያርጋል፤

10/ በታክስ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያቀረበው ግለሰብ ወይም ድርጅት ቅሬታው ቀርቦ እየታየ መሆኑ ተገልጾ እንዲሰጥ በቅሬታ አቅራቢው ሲጠየቅ እንደ አስፈላጊነቱ ለሚመለከታቸው አካላት በጽሑፍ ይገልፃል፤

11/ በጽ/ቤት ኃላፊ የሚሰጡ ሌሎች ሥራዎችን ያከናውናል፡፡

## 11. የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት የውሳኔ ሐሳብ አቀራረብ እና የውሳኔ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት

1/ እያንዳንዱ የታክስ ውሳኔ ቅሬታ በሚሰማበት ጊዜ ከቡድኑ አባላት ሦስት ባለሙያዎች ወይም የአባላቱ ሁለት ሦስተኛ ከተገኙ ምልዓተ-ጉባዔው እንደተሟላ ተቆጥሮ የታክስ ውሳኔ ቅሬታ መሰማቱ ይቀጥላል፡፡

2/ በተሟላ ምልዓተ-ጉባዔ ታይቶ በአብላጫ ድምጽ የተደገፈው የውሳኔ ሐሳብ የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ቡድን የውሳኔ ሐሳብ ይሆናል፡፡ ድምፁ እኩል የተከፈለ እንደሆነ በጽ/ቤት ኃላፊው ወይም በሰብሳቢው የተደገፈው ሐሳብ የታክስ ቅሬታ አጣሪ ቡድን የውሳኔ ሐሳብ ይሆናል፡፡

3/ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በውሳኔ ሐሳብ አሰጣጡ ከአብላጫው ድምጽ የተለየ ሐሳብ ያለው አባል የተለየበትን የውሳኔ ሐሳብ ገልጾና ፈርሞ በቃለ-ጉባዔ እንዲመዘገብለት ያደርጋል፡፡

4/ የቅ/ጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ ወይም በሥራ አስኪያጁ የተወከለው የሥራ ኃላፊ የታክስ ሕጉን መሰረት በማድረግ በአብላጫ ድምፅ የቀረበውን ወይም በልዩነት የቀረበውን የውሳኔ ሐሳብ ሊያፀናው፣ ሊያሻሽለው ወይም በአወሳሰኑ ላይ አቅጣጫ በመስጠት ወደ ጽ/ቤቱ ሊመልሰው ይችላል፡፡

5/ በቡድኑ የቀረበው የውሳኔ ሐሳብ በቅ/ጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ ወይም በሥራ አስኪያጁ በተወከለው የሥራ ኃላፊ ተሻሽሎ ከተወሰነ ገዥ የሚሆነው የተሻሻለው ሆኖ በቡድኑ የቀረበው የውሳኔ ሐሳብ ተመዝግቦ ሊቀመጥ ይገባል፡፡

6/ በታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት የሚቀርበው የውሳኔ ሐሳብ በቅ/ጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ ወይም በሥራ አስኪያጁ በተወከለው የሥራ ኃላፊ በዚህ አንቀጽ ንዑስ 4 መሰረት ሲወሰን የመጨረሻ ውሳኔ ይሆናል፡፡

## 12. የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ቡድን የውሳኔ ሐሳብ

1/ የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት የሚያቀርበው የውሳኔ ሐሳብ በታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 54 መሠረት፣

ሀ/ የቅሬታውን መነሻ ምክንያት፣

ለ/ ቅሬታውንና በሁለቱም ወገን የተደረገውን ክርክር፣

ሐ/ ውሳኔ የሚያስፈልጋቸውን ጭብጦች፣

መ/ ትንታኔዎች፣

ሠ/ ከውሳኔ ሐሳብ ላይ ለመድረስ ያስቻለውን ሕግና ምክንያት እንዲሁም ማስረጃዎችን የያዘ መሆን አለበት፡፡

2/ የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት ውሳኔ ለመስጠት አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ከማንኛውም ሰው ማንኛውንም ዓይነት ማስረጃ እንዲቀርብለት በጉዳዩ ላይ የውሳኔ ሐሳብ ከማቅረቡ በፊት የሚመለከተውን ሰው ወይም አካል መጠየቅ ይችላል፡፡

3/ ከኦዲት የሥራ ክፍል ወይም ከሌላ የታክስ ውሳኔውን ከሰጠው የሥራ ክፍል የማቅረቢያ ጊዜያቸው ተገልጾ እንዲቀርቡ የሚፈለጉ ማብራሪያዎች ወይም የታክስ አወሳሰን ሪፖርቶች ወይም ለቀረበው ቅሬታ መልስ ለታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት መቅረባቸውን ይከታተላል፣ያረጋግጣል፡፡

4/ የዚህን አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ያላከበረ የኦዲት ወይም የሚኒስቴሩ ሌላ የሥራ ክፍል ኃላፊ ወይም ባለሙያ እንደሁኔታው በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ተቋማዊ ስጋት ሥራ አመራርና ሥነ-ምግባር ሊጠየቅ ይችላል፡፡

5/ የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት በማንኛውም ሁኔታ ሌሎች የሥራ ክፍሎች ጽ/ቤቱ በያዘው የታክስ ውሳኔ ቅሬታ ላይ አጣርተው ውሳኔ እንዲሰጡ ጉዳዩን ማስተላለፍ አይችልም፡፡ በዚህ መልክ እንዲወሰን ተላልፎ የሚሰጥ ቅሬታ ላይ የተሰጠ ውሳኔ እንደ ውሳኔ አይቆጠርም፡፡

6/ የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ከመስጠቱ በፊት ያልቀረበ ማስረጃ ለታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት ማስረጃው እንዳለ በታክስ ከፋዩ ከተገለጸ ጽ/ቤቱ ማስረጃውን ተቀብሎና አረጋግጦ ውሳኔ መስጠት አለበት እንጅ "ማስረጃው ተረጋግጦ ይወሰን" በማለት የውሳኔ ሐሳብ መስጠት የለበትም፡፡

7/ ለታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት በቀረበ የታክስ ውሳኔ ቅሬታ ላይ ውሳኔ ቢሰጥም ከታክስ ውሳኔው ጋር በተያያዘ ሐሰተኛ ሰነድ ጥቅም ላይ ከዋለ፤ ከፍተኛ የሆነ ጉዳት የሚያስከትል ግልጽ ስህተት ከተፈጸመ ወይም ወንጀል ጠቀስ ተግባርን መሰረት በማድረግ የተሰጠ የታክስ ውሳኔ ከሆነ ወንጀሉ በሚመለከተው አካል ተጣርቶ የሚወሰደው እርምጃ እንደተጠበቀ ሆኖ ሚኒስትሩ በማንኛውም ጊዜ በቅሬታ ላይ የተሰጠውን ውሳኔ ወይም ለታክስ ከፋዩ የተሰጠውን የታክስ ስሌት በማሻሻል ወይም በመሻር ለታክስ ከፋዩ የተሻሻለ የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ በፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ መሰረት እንዲሰጠው ሊወስን ይችላል፡፡

8/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 አፈጻጸም ሚኒስትሩ ተገቢ ነው ብሎ ሲያምን በጉዳዩ ላይ የውሳኔ ሐሳብ የሚያቀርብ ጊዜያዊ የባለሙያዎች ቡድን ሊያቋቁም ወይም ተገቢነት ያለው የሥራ ክፍል ጉዳዩን መርምሮ የተሻሻለ የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ እንዲሰጥ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

9/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 መሰረት ውሳኔው እንዲሻሻል በማድረግ ሂደት የተወሰደው ጊዜ በታክስ ቅሬታ ላይ በተሰጠ ውሳኔ ላይ ይግባኝ ለማቅረብ በሕጉ የተቀመጠው ጊዜ መቆጠርን የሚያስቀር አይሆንም፡፡

## ክፍል አራት

## በታክስ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ስለማቅረብ

### 13. የታክስ ውሳኔ ቅሬታ ስለማቅረብ

ማንኛውም ታክስ ከፋይ በተወሰነበት የታክስ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ካለው እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ (14) እና (15) የተመለከቱትን ግዴታዎች ካሟላ በታክስ ውሳኔው ላይ ቅሬታ ማቅረብ ይችላል፡፡

### 14. የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አቀራረብ

1/ የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አቅራቢው በታክስ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ካለው የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያው ከደረሰው ቀጥሎ ካለው የሥራ ቀን ጀምሮ በሚቆጠር ሃያ አንድ ቀናት ውስጥ የታክስ ውሳኔ ቅሬታ ማመልከቻውን በቅ/ጽ/ቤቱ ለታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት ማቅረብ አለበት፡፡

2/ ታክስ ከፋዩ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ቅሬታውን ሳያቀርብ የቅሬታ ማቅረቢያ ጊዜ ያለፈበት እንደሆነ በአዋጁ መሠረት ጥያቄውን በጽሑፍ ለታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት አቅርቦ የቅ/ጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ ወይም እሱ የወከለው ሰው ሲፈቀድ የጊዜ ማራዘሚያ የቅሬታ ማቅረቢያ ጊዜው ካበቃበት ቀን ጀምሮ ቢበዛ አስር ቀናት ሊሰጠው ይችላል፡፡

### 15. የታክስ ውሳኔ የቅሬታ ማመልከቻ ይዘት

በታክስ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ታክስ ከፋይ ቅሬታውን ሲያቀርብ የሚከተሉትን ያሟላ መሆን አለበት፡-

1/ ታክስ ከፋዩ የሚያቀርበው የቅሬታ ማስታወቂያ የቅሬታውን ፍሬ ነገር እና ምክንያቶች የያዘ መሆን አለበት፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ/1/ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ቅሬታ አቅራቢው፡-

ሀ/ የቅሬታ አቅራቢውን ሥም፣ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር እና አድራሻ፣

ለ/ ቅሬታ የቀረበበትን የታክስ ውሳኔ ይዘት፣

ሐ/ ውሳኔው የተሰጠበትን ቀን፣

መ/ ውሳኔ የሰጠውን ቅ/ጽ/ቤት እና

ሠ/ ሌሎች ለውሳኔ የሚረዱ ፍሬ ነገሮችና ማስረጃዎችን መግለጽ አለበት፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ቅሬታ አቅራቢው የንግድ ፍቃድና የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር የምስክር ወረቀት እንዲሁም ጉዳዩ በታክስ ወኪሉ የሚቀርብ ከሆነ ለወኪሉ ቅሬታ አቅራቢው ውክልና የሰጠበት ማስረጃ እና ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ከሆነ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ማቅረብ አለበት፡፡

4/ የቀረበውን የቅሬታ የሚያስረዱ አግባብነት ያላቸው ሌሎች የሰነድ ቅጅ (ኮፒ) ማስረጃዎች ከዋናው ጋር እንዲገናዘቡ ከቅሬታ ማመልከቻቸው ጋር በአባሪነት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

5/ የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አቅራቢው የሚያቀርበው ቅሬታ ባልተስማማበት የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ላይ እንጅ በተስማማበት የታክስ ስሌት ላይ ስላልሆነ በታመነበት ላይ መከፈል ካለበት ሊከፈል ይገባል፡፡

16. <u>የታክስ ውሳኔ ቅሬታ ማመልከቻ የሚቀርብበት ቀንና አቀራረብ</u>

1/ የቅሬታ ማመልከቻው በቅሬታ አቅራቢው ወይም በሚወከለው የታክስ ወኪል ተፈርሞ የገቢ ማህተም ተደርጎበት ለታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት ሪከርድ ሥራ አመራር ባለሙያ መቅረብ አለበት፡፡

2/ የቅሬታ ማመልከቻው በቅሬታ አቅራቢው እንደቀረበ የሚቆጠረው የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የገቢ ማህተም በተደረገበት ቀን ነው፡፡

17. <u>በቅሬታ ላይ ውሳኔ የሚሰጥበት የጊዜ ገደብ</u>

1/ በታክስ ውሳኔ ቅሬታ ላይ ታክስ ከፋዩ ላቀረበው ቅሬታ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ቅሬታው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉት አንድ መቶ ሰማንያ ቀናት ውስጥ ለቅሬታው ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ሚኒስቴሩ ውሳኔ ካልሰጠ ቅሬታ አቅራቢው የአንድ መቶ ሰማንያ ቀናት ጊዜ ገደብ ከተጠናቀቀበት ቀን ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

3/ በቀረቡ ቅሬታዎች ላይ ጽ/ቤቱ ለተጨማሪ የማጣራት ሥራ ውሳኔውን ለወሰነው የሥራ ክፍል የሚሰጠው ጊዜ ከአንድ ወር መብለጥ የለበትም፡፡

## ክፍል አምስት

18. <u>የተሻሩና ተፈፃሚነት የሌላቸው መመሪያዎች</u>

1/ የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት የአሠራር መመሪያ ቁጥር 169/2012 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

2/ ቀደም ሲል የነበሩ አሠራሮች ይህን መመሪያ የሚቃረኑ ከሆነ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

19. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች</u>

ይህ መመሪያ ተፈጻሚ ከመሆኑ በፊት ለጽ/ቤት የቀረበ እና ውሳኔ ያላገኘ የታክስ ውሳኔ ቅሬታ በቀረበበት የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት በዚህ መመሪያ መሠረት ውሳኔ ያገኛል፡፡

20. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ ከታህሳስ 1 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ታህሳስ 2013 ዓ.ም

ላቀ አያሌው

የገቢዎች ሚኒስቴር ሚኒስትር